## አስናቀ እንግዳ ይድረስህ ምስጋና

*(ነሀሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም. በአሲምባ ፓል ቶክ በአሉላ የቀረበ)*

https://www.youtube.com/watch?v=zl6w24SgunI



ጥር 07 1906 - ግንቦት 21 2009

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሸክሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን የኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ደጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

ያገር ፍቅር ስሜት ውስጡን እየበላው
የወገኑ ብሶት እያብከነከነው
የሰንደቁ ክብር እያንገበገበው
ኢትዮጵያ ታሪኳ ተከብሮ እንዲኖር
አንድነቷ ጸንቶ እንዲሆነን ማገር
ሉዓላዊነቷ ጸንቶ እስከዘላለም
የሕዝቧ አንድነት እንዲኖር እስካለም
ታግሎ ያታገለ፡ መካሪ የረቀቀ
ከቶ ወዴት አለ? እንዳተ አስናቀ።

የግፍ አገዛዝን፡ ጭቆና ምዝበራ
መከራና እምባ ከቶ እንዲያባራ
ከአድሞአችን እንዲጠፋ በሽታና ረሃብ
ዕድሜህን የኖርከው ቆመህ ለሀገር ዘብ
እኮ የት ይገኛል? ይህን ሁሉ ዘመን
ከቶ ሳይሰለች ለሕዝብ ሲብከነከን።
አሟጦ የሰጠ ሕይወቱን ለሀገር
ለፊውዳል ጥሪ ፊቱንም ሳያዞር
በፋሽስቶች ሴራ ላፍታ ሳይሸበር
በጎጠኞች ወጥመድ ከቶ ሳይበገር
በሀገር ጠላቶች ቅስሙ ሳይሰበር
በጽናት የቃኘ የሀገርን ዳር ድንበር
ከቶ የት ይገኛል? የሀገር ወታደር።

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሸክሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን የኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ደጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

ጸንተህ የታገልህ ሦስት የመከራ ዘመን
ጨለማ ተገፎ፡ እንዲሰፍን ብርሃን
ተዋጊ ባርነት፡ ነፃነት አፍቃሪ
ሀገርህን ወዳድ፡ ጠላት አሳፋሪ
ጠላት አባራሪ
ለፊውዳል ቅኝት፡ ለቡርዣ ከበሮ
ለስምና ዝና፡ ለተጫፍሮ ኑሮ
ለክብር ለንዋይ፡ ሳትሰጥ ቀጠሮ
እንዳሰማህ ያለህ የሕዝብን ሮሮ
እንደማሰንክ ኖረህ ጋራ ሸንተረሩን፡
ቋጥኙን እሾሁን፡
ደጋውን ቆላውን፡
ይዘህ ተሸከመህ ብሶት መከራውን
አታግለህ የታገልክ፡ ቆፍጣናው ኮሎኔል
እኔስ ኩራሁ ባንተ፡ እስቲ ዕልል ልበል።

ብርታትህን ሳየው፡ ተስፋዬ ጠነከረ
መላውን ዕድሜህን ወኔህ ያልሰበረ
እምቢኝ ለጎጠኛ ብሎ ዛሬም አለ
እጅ አልሰጥ ለጠላት፡ ከቶም ለቀለለ
ነፃነቴን ብሎ አለ እንደታገለ።
እስቲ ላመስግንህ እንግዳው አስናቀ
ፍቅር የሀገርህ ምስጥሩ የረቀቀ።

"ከበታኝ ወያኔ ከቶም ላላስካካ
በባዕዳን ሽምገላ ፍጹም ሳልመካ
ክብሬን የጠበኩኝ ከመሰሪ ደባ
ለውሸት ላላድር፡ ላለብስ ሀሰት ካባ

ጥጋብ ተሞሽሮ፡ ረሃብ ስፍራ አጥቶ
ብልጽግና አብቦ፡ ድህነት ተንኮታኩቶ
ጤናና ደስታ፡ በበሽታ ስቀው
ይደንቁር አባቱ ድንቁርና ጠፍቶ
ጎሰኝነት ሞቶ፡ አንድነት አብበ
ባርነት ተገፎ፡ ነፃነት ተውበ
ክብሯን አስጠብቄ፡ ሀገሬን እምዬ
ምድሪቷንም ስሜ፡ ዘልቄ ከቀዬ
ሰንደቅ ዓላማዋን ይገፔ፡ ከማማ ላይ ቆሜ
ማየትን እሻለሁኝ፡ በቀሪዋ ዕድሜ . . .”
ብለህ ያወጋኸኝ፡ አስናቀ አባቴ
“አክሊሌም ይኸው ነው፡ መስቀሌ ጽናቴ”
ብለህ ያስተማርከኝ፡ “ይኸው ነው ሕይወቴ”
ዛሬ ልተርከው አውጥቼ ካንጀቴ።

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሽከሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን የኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ድጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

ፈደል መቁጠር ብቻ እኮ ዋጋ ካለው
ጮርቃ ያልበሰለ፡ ዕውቀትም ቢኖረው
ዐዋቂ ነው ተባይ፡ ብርቱ ሚመራመር
ሀገሩን የማያውቅ፡ ሲጠሩት ግን በክብር
ስንቱን ያስነበበ፡ ስንቱን ተፈላስፎ
ሀገር ሲሉት ባዶ፡ ሕዝብ ሲሉት ቀፎ
ይምጣና ይመርምር፡ እዚህ ግኝት አለ
ሳይንስ የማያውቀው፡ ጽናት የተባለ
ዕድሜውን ከሚፈጅ ወሬ እያነጠረ፡ ወሬ እያጠለለ።

ይምጣ ይስተናገድ ካስናቀ ኮሌጅ
ተምሮ ደንቁሮ፡ ለሀገር የማይበጅ
ሀገሩን ይወቃት፡ አይሁንባት ባዳ
አይናቀው፡ አያጥላላው፡ ሕዝቡንም ይረዳ
ያጥብቀው፡ ከፍ ያርገው ያገሩን ባንዲራ
ተምሮ ካስናቀ፡ ከዚህ ከደብተራ
ከሀገር አባ ወራ።

ሦስት መንግሥት ካዬ፡ ከዓፄው ጀምሮ
እየተገላበጠ ደልቆ ከበሮ፡ ከሁሉም ጋር አድሮ
ከዓፄው ጋር ሆኖ፡ በረሃብ የሳቀ
በበሽታ፡ ድህነት፡ ከቶ የተሳለቀ
ከደርግም አገዛዝ፡ ሄዶ የተጣበቀ
እናት ሀገር ብሎ፡ በሀገር የቀለደ
መኖር ነው እያለ፡ ዳር ዳሩን የሄደ
ወያኔም ሲመጣ፡ እጁን የሰደደ
በሦስቱም አገዛዝ፡ ሆዱን የወደደ
በሀገር አሹፎ፡ በሕዝብ ያላገጠ
እኔስ አፈርኩበት፡ ተማርኩ ያለ ደንቆሮ
ኑሮው የቀበሮ
አደባባይ ወጥቶ፡ ከሚሆን ቀዳዳ
መሄጃው ጠፍቶበት፡ ከሚሄድ ገዳዳ
ይልቁንስ ይማር፡ ካስናቀ እንግዳ
መንገድ ያሳየዋል፡ የሀገሩን ጓዳ።

ሦስት መንግሥት ታግሎ፡ ታሪኩ ሚጻፈው
አንደበተ ርቱዕ፡ ቆራጥ ለዓላማው
ዘላለም ዓለሙን፡ ከሕዝብ ጋር ያለው
አስናቀ እንግዳ፡ ብዙ ትምህርት አለው።

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሽከሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን የኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ድጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

አንጋፋ በዕድሜ፡ ባገኝህም ሆነህ
ኮነሌሉ ቀርቶ፡ እምዬ ልበልህ
ማዕረጉን ልተወው፡ አብዬ እንድልህ
መከታ ጋሻዬ፡ እንበልህ ያገሬ
በተግባር ተፈትነህ፡ የቆምከው ከበሬ
ቃላቶች የሉኝም እኔ ላንተ ክብሬ።
አውርሰኝ ቃል ኪዳን፡ ልገዛ በቃልህ
ባርከህ ስጠኝ አርማ፡ እስቲ በለኝ አይዞህ
በርከክ ብዬ ልውሰድ፡ ልጎንበስ ከግርህ
ልደፋ ከግርህ።

ግጥሙን በድምጽ ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ፡-
https://www.youtube.com/watch?v=zl6w24SgunI
alulla2@yahoo.com